ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፪፣ ቁጥር ፯ ፣ ታህሳስ ፳፻፲፬ ዓ.ም

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ በሚል ርዕስ በየሁለት ወሩ በአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን እየተዘጋጀች የምትሰራጨው ይህቺ ዜና መፅሄት የኢትዮጵያን በፈቃደኛነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ ለመቀነስ የተዘጋጀውን ዕቅድና አፈፃፀሙን በተመለከተ መረጃዎችንና አዳዲስ እውቀቶችን ለተለያዩ ባለድርሻዎች የማድረስ ዓላማ አላት።



“የኢትዮጵያ ፖሊሲዎች ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ልማት ስልት ላይ የተመረኮዙ በመሆናቸው አረንጓዴ ቴክኖሎጂዎችን ያበረታታሉ”

የደን እና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ኮሚሽነር ክቡር ፕ/ር ፈቃዱ በየነ

በዚህ እትም. . .

ከኢትዮጵያ ፍላጎት አንፃር የኮፕ 26 ዋነኛ ውጤቶች ፪

ዜናዎች ፪

ሁነቶች ፯

ከ26ኛው ዓለም ዓቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ ጎንዮሽ የነበረው የኢትዮጵያ ተሳትፎ ዳሰሳ - የፓሪስን ግቦች ከማሳካት አኳያ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና የመሬት አጠቃቀም ሚና ፯

ልዩ ልዩ ሀትመቶች ፯



ዋና አዘጋጅ፥ ንጉሱ ለማ ገብሬ

አዘጋጆች፥ ተስፋዬ ጋሻው፣ ሙሉነህ ገ/ሄደቶ፣ በእምነት ተሾመ እና ሮቢ ረዳ

አምደኞች፥ መንሱር ደሴ እና መሀመድ አንዶሼ

ግራፊክስና ሌይአውት፥ አርሴማ አንዳርጋቸው

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፪፣ ቁጥር ፮

ዜናዎች

"ጊዜው የምንናገረውን ሆነን መገኘት ያለብን ወቅት ነው!" በ26ኛው የተ.መ.ድ. የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ ላይ የኢትዮጵያ መልዕክት

እ.አ.አ. ኖቬምበር 10/2021 ከአለም ዙሪያ የመጡ የሀገራት የአካባቢ ሚኒስትሮች በ26ኛው የተ.መ.ድ የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ ላይ ሀገራዊ መግለጫዎችን ሰጥተዋል። ኢትዮጵያን በመወከል በመድረኩ ላይ ንግግር ያደረጉት የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽነር ክቡር ፕ/ር ፍቃዱ በየነ ለአለም አቀፉ ማህበረሰብ ባሠሙት ንግግር "የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳይን አስመልክቶ ሁላችንም የምንናገረውን ሆነን መገኘት ይገባናል" ብለዋል። በተጨማሪም ኮሚሽነሩ "ሁላችንም የምንወቅሰው የተለየ አካል፤ እቅዳችንን ለጥጠን ላለማቀድና ላለመተግበር የምናቀርበው ሰበብ ሊኖር አይገባም" ብለዋል። ክቡር ኮሚሽነሩ በንግግራቸው አክለው እንደገለፁት ሳይንሳዊ መረጃዎች የዓለም ሙቀት መጠን በ1.1 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ መሞቁን በግልፅ ቢያሳይም የአለም ማህበረሰብ ለዚህ ችግር ምላሽ ለመስጠት በትክክለኛው መንገድ ላይ እንዳልሆነ ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያ በ2030 በተለመደው ሁኔታ ቢኬድ ሊደረስበት ከሚችለው የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት 69% የሚሆነውን የሙቀት አማቂ ጋዞችን ልቀትን ለመቀነስ የሚያስችላትንና በመስኩ ከቀረቡ ዕቅዶች በጣም የተለጠጠ የሚባለውን በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ መቀነሻ ዕቅድ ይፋ ማድረጓን ክቡር ኮሚሽነሩ ገልፀዋል። ኮሚሽነሩ በንግግራቸው መጨረሻ የኢትዮጵያ "አረንጓዴ አሻራ" ብላ በሰየመችው የችግኝ ተከላ ፕሮግራም እ.አ.አ እስከ 2022 ሀያ ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል ማቀዷንና ባለፉት ሶስት የክረምት ወራት ከ15 ቢሊዮን በላይ ችግኞችን መትከል መቻሉን ገልፀው ይህም ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥን አሉታዊ ተፅዕኖ ለመግታት ከዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ጋር በጋራ ለመስራት ያላትን ቁርጠኝነት እና ተግባራዊ ምላሽ የሚያሳይ ነው ብለዋል።

ለዜሮ ልቀትና የአየር ንብረት አሉታዊ ተፅኖን ለመቋቋም የጋራ ትብብር

ከግላስጎው የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ ጎን ለጎን ከተከናወኑ ሁነቶች አንዱ "ለዜሮ ልቀትና የአየር ንብረት አሉታዊ ተፅኖን መመቋቋም" ትብብር የኢትዮጵያና የቻይና ተሞክሮዎች በሚል ርዕስ የተካሄደው ሁነት ይገኝበታል። በሁነቱ ላይ ኢትዮጵያ የመሬት መራቆትን ለመቀነስ፣ የአየር ንብረት ለውጥን ለማጣጣምና ለማስተሰረይ እንዲሁም የምግብ ዋስትናን እና የመሬት ምርት ሰጪነት ለማሻሻል ከ2005 ዓ.ም የተሠሩ ስራዎችን መልካም ተግባሮች ተሞክሮ አካፍለለች።

በመድረኩ ላይ የቻይና የባህር ማዶ የሀይል ኢንቨስትመንት ታዳጊ ሀገራት አረንጓዴ እና ዝቅተኛ የካርቦን ሃይልን ለማምረትና አዳዲስ የድንጋይ ከሰል ሃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶችን ለመቀነስ የቻይና መንግስት በቅርቡ ይፋ ባደረገው ፕሮግራም መሠረት እየተከናወኑ ያሉ ድጋፎችን የተዳሰሰበት መድረክ ነበር። የቻይና ኢንቨስትመንት እስካሁን በአስተናጋጅ ሀገራት ፍላጎት ላይ በተመሰረተ ሁኔታ ተፈፃሚ እየሆነ እንደሚገኝና ለዚህም ኢትዮጵያ በዚህ የኢንቨስትመንት ድጋፍ በርካታ የታዳሽ ሃይል አማራጮች እያለማችና ለአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ ቅነሳ ተስማሚ የሆነ የኢነርጂ ልማት ከፍተኛ ድጋፍ ካገኙ ሀገራት ጥሩ ምሳሌ ተደርጋ መታየቷ በውይይቱ ተነስቷል። በተጨማሪም በመድረኩ ቻይና በዓለም አቀፍ ደረጃ የታዳሽ ሃይልን ልማትና ድጋፍ በከፍተኛ ደረጃ ለመደገፍና ዝግጁ መሆኗ ተገልጿል። ምንጭ

ከኢትዮጵያ ፍላጎት አንፃር የኮፕ 26 ዋነኛ ውጤቶች

❑ በአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን

የኢትዮጵያ ለአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ቁርጠኝነት የጀመረው እ.ኤ.አ በ1992 የተቋቋመውና ኢትዮጵያም የተፈራረመችበት የተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ማዕቀፍ ኮንቬንሽን (UNFCCC) ጅማሬ አንስቶ ነው። ኢትዮጵያ በየአመቱ በሚካሄደው የአባል ሀገራት ኮንፈረንስ ላይ መካፈልዋ ከሀጋዊ ተሳትፎነት የዘለለ ሲሆን፤ በUNFCCC ሂደት ከምስረታው አንስቶ የመሪነት ሚና ተጫውታለች። ኢትዮጵያ የታዳጊ ሀገራት ቡድንን እ.ኤ.አ ከ2016-2018 የመራች ሲሆን አሁንም ቡድኑን የተለያዩ የቴክኒካልና ከፍተኛ ደረጃ ውይይቶችን በመምራት ታግዛለች። በተጨማሪም ለአየር ንብረት ተጋላጭ ፎረምን (CVF) ከ2016-2018 በሊቀመንበርነት የመራች ሲሆን በአሁን ወቅትም የCVF ትሮይካ አባል ናት። ኢትዮጵያ ከዚህ በተጨማሪ የአፍሪካ ሀገራት መሪዎች ኮሚቴንና የአየር ንብረት ለውጥ መንግስታት ጉባኤ (CAHOSCC)ን በኮፐንሀገን ከታካሄደው COP15 አንስቶ መርታለች። የ CAHOSCC ሊቀመንበር የነበሩትም በኮፐ 15 የበለፀጉት ሀገራት ለታዳጊ ሀገራት ለአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ትግበራ የሚያግዝ የ100 ቢሊዮን ዶላር ልገሳ በ2020 እንዲያደርጉ ከፍተኛውን ሚና ከተጫወቱት አመራሮች መሀል ነበሩ።

ጣልያንና ዩናይትድ ኪንግደም በጋራ ያዘጋጁት COP26 በግላስጎው ስኮትላንድ እ.ኤ.አ ከጥቅምት 31-ህዳር 12፤ 2021 ድረስ ተካሂዷል። ኢትዮጵያ በዚህ ኮንፈረንስ ላይ ንቁ ተሳታፊ የነበረች ሲሆን ይህም ፅሁፍ ከኢትዮጵያ ፍለጎት አናፃር የCOP26ን ውጤቶች ይቃኛል።

ኢትዮጵያ ከCOP26 የጠበቀቻቸው ውጤቶች

- ፋይናንስ ማፈላለግና አጋርነትን ማጠናከር።
- የፓሪስ ስምምነት መተግበሪያ ደንብን ማጠናቀቅ።

ወደ ገፅ ፫

ከገፅ ፪ የቀጠለ

- ከ2020-2024 በየአመቱ ለአየር ንብረት ትግበራ ካደጉ ሃገራት ቃል የተገባውን የ100 ቢሊዮን ዶላር ልገሳ ማጠናከር።
- አባል ሀገራት የተሻሻለ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ (NDC) ለUNFCC ማስገባትን።
- ለማጣጣሚያ ትግበራ ተጨማሪ ሀብት መመደብና ለማጣጣሚያና ማስተሰረያ የሚመደብ ሀብት ሚዛናዊ እንዲሆን ማድረግ።
- የተሻሻለ የግልፀኝነት ማዕቀፍ ላይ የሚደረጉ ውይይቶች መጠናቀቅ።
- በአቅም ግንባታና የቴክኖሎጂ ፍሰት ማደግ ላየ ቁርጠኝነት ማሳየት።

2. የCOP26 ዋነኛ ውጤቶች

የCOP26 ዋነኛ የፖለቲካ ውጤት የግላስጎው የአየር ንብረት ስምምነት ተብሎ ሲሰየም መንግስታት ከፓሪስ የሙቀት ቅነሳ ስምምነት ግብ ጋር በተጣጣመ መልኩ የአየር ንብረት ዕቅዳቸውን (NDC) እ.ኤ.አ ከ 2022 ማለቂያ በፊት እንዲከልሱ ይጠይቃል። የአለም ሙቀት ከ1.5°C የበለጠ እንዳይጨምር መንግስታት በግብፅ ሻርለም ሼክ ከሚካሄደው ኮፕ 27 በፊት የተለየ ቁርጠኝነት የሚያሳይ የአየር ንብረት ዕቅድ ይዘው መምጣት ይጠበቅባቸዋል። የግላስጎው የአየር ንብረት ስምምነት ሌላው ገፅታ የድንጋይ ከሰል ሃይል አጠቃቀምን መቀነስ እና ቅሪተ አካልን ለነዳጅ ለመጠቀም የሚመደበውን ድጎማ ማሰወገድ ናቸው። የግላስጎው ሰሚት በክላይሜት ፋይናንስ፣ በማጣጣሚያ እና ኪሳራና ጉዳት ዙሪያ የተሻለ ዕቅድ ለማስቀመጥ እንዲሁም የፓሪስ ስምምነትን ለመተግበር የሚያግዙ ህጎች እንዲጠናቀቁ እድል ፈጥሯል።

2.1 የማስተሰረያ (Mitigation) ትግበራና ልኬት

ለNDC የጋራ ማዕቀፍ

የአሁኑ NDC የፓሪስ የ1.5°C ግብን ከማሳካት ረገድ ክፍተት አለበት። በቅርብ በተደረገ የUNFCCC የNDC ምዘና ሪፖርት መሰረት የሀገራት የአሁኑ NDC ግብ የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀትን ከጊዜ በኋላ በ16% እንዲጨምር ያደርገዋል። ስለዚህ ሀገራት ዕቅዳቸውን እ.ኤ.አ እስከ 2030 ከሚደረገው የአለም አቀፍ የሙቀት አማቂ ጋዝ ቅነሰ ልኬት ግምገማ በፊት ከፓሪስ ስምምነት አንቀፅ 4 ግዴታዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ መከለስ አለባቸው።

የCOP26 ውጤቶች፡ ሀገራት እ.ኤ.አ በ 2025፣ ከ2025-2035 የሚሸፍን NDC እንዲያዘጋጁ እንዲሁም በየ5 ዓመቱ የአስር ዓመት ዕቅዳቸውን እንዲያስገቡ ይበረታታሉ።

2.2 ፋይናንስ

ከፍተኛ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ እያረፈባቸው የሚገኙትና፣ ልቀትን ለመቀነስና ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ የሚያስችል የፋይናንስ እጥረት ያለባቸው ታዳጊ ሀገራት የአየር ንብረት ለውጥ ፋይናነስ ዋነኛ ቅድመ ሁኔታቸው ነው።

በCOP26 ታዳጊ ሀገራት የበለፀጉት ሀገራት ለአየር ንብረት ትግበራ ቃል የገቡትን ፋይናንስ ባለመልቀቃቸው ያደረባቸውን ቅሬታ የገለፁ ሲሆን በዚህም የተነሳ መተማመናቸው እንደተሸረሸረ አስምረውበታል። ከዚህም በተጨማሪ የአየር ንብረት ለውጥ ፋይናንስ ከ100 ቢሊዮን ዶላር በላይ ማደግ እንዳለበት ገልፀዋል። ምንም እንኳን አንዳንድ ሀገራት አዲስ ቁርጠኝነት ይዘው የመጡ ቢሆንም፤ ይህ ግብ መቼ እንደሚሳካ ግን ግልፅ አይደለም። የግላስጎው የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነት ጥልቅ በሆነ ፀፀት የ100 ቢሊዮን ዶላር ቃል አለመሳካቱን በመግለፅ ያደጉት ሀገራት ይህን ቃል በ2025 እንዲያሳኩት ጠይቋል።

2.3 የፓሪስ ስምምነት አንቀፅ 6

የፓሪስ ስምምነት አንቀፅ 6 የሚያተኩረው አለም አቀፍ የካርቦን ግብይትን ማሳደግ ላይ ሲሆን ይህም የሃይል ሽግግርን ለማሳለጥና የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀትን ለመቀነስ ይረዳል። በCOP26 አንቀፅ 6ን በማፅደቅ አለም አቀፍ የካርቦን ግብይትን ማዕቀፍን በመፍጠር ረገድ ስኬት ተመዝግቧል።

2.4 የማጣጣሚያ (Adaptation) ትግበራና ልኬት

የማጣጣሚያ ኮሚቴው ሪፖርት

የማጣጣሚያ ኮሚቴው በስሩ በተቋቋሙት ንዑስ አካላት በኩል በየአመቱ ለCOP ሪፖርት ያደርጋል። ምንም እንኳን የማጣጣሚያ ኮሚቴው ይህንን ተግባሩን ለማከናወን የተለያዩ ዘዴዎችን እየተጠቀመ ቢሆንም ለዚህ ተብለው የተቀረፁ መሳሪያዎችን ግን ሙሉ ለሙሉ አለመጠቀሙ ግልፅ ነው።

ወደ ገፅ ፬

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፪፣ ቁጥር ፭

ከገፅ ፫ የቀጠለ

ከዚህ በተጨማሪ ኮሚቴው የተለያዩ ከቡድኑ ውጪ ያሉ ባለሙያዎችን በተወሰኑ ጭብጦች ዙሪያ በመጋበዝ ውጤታማነቱን ማሻሻል እንዳለበት ተመላክቷል። አባል ሀገራት ከዚህ በተጨማሪ በአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ ዙሪያ ዘርፈ ብዙ ሙያዎች ያሉዋቸው ባለሙዎችን በመምረጥና በማሳተፍ የኮሚቴውን ውጤታማነት መጨመር ይችላሉ።

የCOP26 ውጤቶች: COP የማጣጣሚያ ኮሚቴውን የ2019፣ 2020 እና 2021 ሪፖርት የተቀበለው ሲሆን፤ ሪፖርቱን የመገምገም ስራ ግን ወደ ቀጣዩ COP አስተላልፎታል።

በተፅዕኖ፣ ተጋላጭነትና የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ ላይ የሚያተኩረው የናይሮቢ ስራ ፕሮግራም

በተፅዕኖ፣ ተጋላጭነትና የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ ላይ የሚያተኩረው የናይሮቢ ስራ ፕሮግራም፤ የUNFCCC በማጣጣሚያና አልበገሬነት ስራዎች ላይ ዕውቀትን ወደ ተግባር የመቀየሪያ ማዕከል ነው። የአባል ሀገራት ፍላጎት ከተለያዩ 425 ከሚሆኑና በተለያዩ ጭብጦች ዙሪያ ከሚሰሩ የእውቀት፣ ሙያ፣ ጥምረት፣ ኔትዎርክ፣ ውቅር አካላት፣ ፓርቲዎችና ባለሙያዎች ጋር በመተባበር ምላሽ እንዲያገኝ ተደርጓል።

የCOP26 ውጤቶች: ለኮንቬሽኑ ተጠሪ የሆነው የሳይንስና የቴክኒክ ንዑስ ቡድን (SBSTA) ፤ የናይሮቢ ስራ ፕሮግራምን ሪፖርት የመገምገም ስራ አጠናቋል።

ከታዳጊ ሀገራት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች

የታዳጊ ሀገራት የባለሙያዎች ቡድን (LEG) የተቋቋመው እ.ኤ.አ በ2001 ሲሆን በአሁን ወቅት ለታዳጊ ሀገራት በሀገራዊ የማጣጣሚያ ዕቅድ ዝግጅት ዙሪያ ቴክኒካል መመሪዎች እንዲዘጋጅና ሌሎች ድጋፎችን እንዲያደርግ፣ ሀገራዊ የመጣጣሚያ የድርጊት መርሀ ግብር ፕሮግራም እንዲዘጋጅና እንዲተገበር ድገፍ የመስጠትና የቡድኑን የድርጊት ፕሮግራም የማስተግበር ሀላፊነት ተጥሎበታል። LEG ከዚህ በተጨማሪ ሀገራዊ የማጣጣሚያ ዕቅድን ለመንደፍና ለመተግበር የሚያግዝ ሀብት ከአረንጓዴ የአየር ንብረት ፈንድ (GCF) ለማግኘት የሚያስችል ቴክኒካል መመሪያና ምክር ይሰጣል። በተጨማሪ LEG የስራ ፕሮግራሙን ለመተግበር የሚያግዙ የተለያዩ ድርጅቶችን የማሳተፍ ሀላፊነት አለበት። የLEG ድጋፎች ታዳጊ ሀገራት የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ መስጠት ለሚያደርጉት ጥረት አጋዥ ሁኖ ቆይቷል።

የCOP26 ውጤቶች: COP የLEG ሀላፊነት ለተጨማሪ አሰርት አመታት እንዲቀጥል የወሰነ ሲሆን በመሀሉም አፈፃፀሙ እንዲገመገምና 3 ከታደጊ ሀገራት 1 ደግሞ ከAnnex I በአጠቃላይ 4 ተጨማሪ አባላት እንዲኖሩት ወስኗል። LEG የአሰራር ደንቦቹን እንዲቀርፅ የተጠየቀ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ አባል ሀገራት የሚቀያየሩብትንም መንገድ እንዲያስቀምጥ ተጠይቋል።

ሀገራዊ የማጣጣሚያ ዕቅድ

COP25 የትግበራ ንዑስ የሳይንስ ቡድን (SBI) በACና LEG ሪፖርት ላይ፣ ሀገራዊ የማጣጣሚያ እቅድ ትግበራ ዙሪያ እንዲሁም የተለዩ ክፍተቶችና ፍላጎቶችን ጨምሮ እንዲወያይ እና አስፈላጊ እርምጃዎችን እንዲወስድ ጠይቆ ነበር።

የLDC ግሩፕ በሀገራዊ የማጣጣሚያ ዕቅድ ዙሪያ ሶስት የመወያያ ነጥቦች የለየ ሲሆን እነዚህም፡ 1) ሀገራዊ የማጣጣሚያ ዕቅድን ለመንደፍ የሚያስፈልግ ድጋፍ 2) ሀገራዊ የማጣጣሚያ ዕቅድን ለመተግበር የሚያስፈልግ ድጋፍ 3) ሀገራዊ የማጣጣሚያ ዕቅድን ለመንደፍና ለመተግበር የተለዩ ፍላጎቶችና ክፍተቶችን መሙላት ናቸው። ቡድኑ ሀገራት በተለያየ ደረጃ ላይ እንደመሆናው መጠን ለሀገራዊ የማጣጣሚያ እቅድ ዝግጅትና ትግበራ የሚደረግ ድጋፍ ሚዛናዊነት ማስጠበቅ አለበት።

የCOP26 ውጤቶች፡ የትግበራ ንዑስ የሳይንስ ቡድን (SBI) በክፍተትና ፍላጎት ዙሪያ ሲያከናውን የነበረውን ጥናት ባለመጨረሱ በቀጣይ ለማየት ውሳኔዎችን አስቀምጧል። SBI ሀገራዊ የማጣጣሚያ እቅዶችን ትግበራ ላይ ግምገማውን ለማጠናቀቅ ችሏል።

አለም አቀፍ የማጣጣሚያ ግብ (GGA)

በ2023 ለሚካሄደው የትግበራ ምዘና ትርጉም ያለው አስተዋፅኦ ለማድረግ አለም አቀፍ የማጣጣሚያ ግብ ስኬት ዙሪያ ያለ መረጃ እንዴት እንደሚገኝ ስምምነት ላይ መድረስ ያስፈልጋል። ውጤታማ በሆነ መልኩ ስኬቶችን ለመለካት ሀሳባዊ፣ ዘዴያዊና የአቅም ጉዳዮችን በአንድነት መፍታት ያስፈልጋል። ይህም የማጣጣሚያ ትግበራን ለመለካት የሚያስችል ዘዴ ለመለየት ራዕይ ማስቀመጥንና ግቡን ለማሳካት የሚያስፈልግ ድጋፍ ማፈላለግን ያጠቃልላል። በሀገራት የተለያየ ሁኔታዎችና ውስብስብ በሆነው የማጣጣሚያ ትግበራ ምክንያት የተለያዩ መለኪያዎችን ብቻ በማስቀመጥ የትግበራን ስኬት መዳሰስ እንደማይቻል የታዳጊ ሀገራት ቡድን ያስቀምጣል። ቡድኑ የተለያዩ ዘዴዎችን ውጤታማነት እርግጠኛ አለመሆን ላይና ከዚህ በጨማሪ የመረጃ እጥረት ላይ የተወያየ ሲሆን እነዚህም እጥረቶች አለም አቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ ግቦች ስኬት ላይ እንቅፋት መፍጠር እንደሌለባቸው ደምድሟል።

ወደ ገፅ ፭

ከገፅ ፬ የቀጠለ

የCOP26 ውጤቶች፡ የፓሪስ ስምምነትን የፈረሙ እና ያጸደቁ ሃገራት የሁለት አመት ግላስጎ-ሻለም ሼክ ፕሮግራም ለመጀመር የተስማሙ ሲሆን፣ ፕሮግራሙ ቀሪዎቹን የ GGA ስራዎች ለማስጀመር የታቀድ ነው።

2.5 የግልፀኝነት ማዕቀፍ

ደረጃውን የጠበቀ የማስተሰረያ ትግበራ የፋይናንስ ሪፖርት ስርዐት ላይ ስምምነት ላይ መድረስ በCOP26 ወቅት ይጠበቅ ነበር። የተሻሻለ የግልፀኝነት ማቀፍን በማጠናቀቅ የፓሪስ ስምምነትን ለመተግበር ውጤቶችን ለመለካትና ለማጋራት የሚያስፈልጉ ዘዴዎች ዙሪያ ስምምነት ላይ ተደርሷል።

አባል ሀገራትም በፓሪስ ስምምነት መሰረት የተሻለ የግልፀኝነት ማዕቀፍን ለመተግበር የሚያስችሉ ሂደቶችን ለመገልገል ስምምነት ላይ ደርሰዋል። ይህም አባል ሀገራት በአየር ንብረት እቅዳቸው መሰረት ያከናወኑትን የልቀት፣ ድጋፍና ትግበራ ሂደትን ለመለካት የሚያስችሉ የተለያዩ ሪፖርት ማድረጊያ ሰንጠረዦችን መጠቀምን ያጠቃልላል።

2.6 ስርዓተ-ጾታ እና የአየር ንብረት ለውጥ

የፓሪስ ስምምነት አንቀፅ 7 እና 11 አባል ሀገራት፣ የሰዎችን፣ የህብረተሰቡን፣ የህጻናትን፣ የአካል ጉዳተኞችንና የተጋላጭ የህብረተስብ ክፍሎችን መብት ማክበር እንዳለባቸው እንዲሁም የጾታ እኩልነትን፣ ሴቶችን ማብቃት እና በትውልዶች መሃል ፍትሃዊነትን ማስፈን እንደሚያስፈልግ ያስቀምጣል። የተዘጋጀው ረቂቅ የስርዓተ-ጾታ የድርጊት መርሀ ግብር 5 ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮችን ያካትታል። እነዚህም፤ የአቅም ግንባታ እና የእውቀት መጋራትና ግንኙነት፤ የስርዓተ-ጾታ እኩልነት፣ ተሳትፎ እና የሴቶች አመራር፤ ቅንጅት፤ ለስርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ ትግበራ እና ግምገማና ሪፖርት ማቅረብን ያጠቃልላሉ።

የCOP26 ውጤቶች፡ አባል ሀገራት ይህን የድርጊት መርሀ ግብር የተቀበሉት ሲሆን በዚህ ዙሪያ ያላቸውንም ስኬት መዝነዋል።

2.7 ኪሳራና ጉዳት

ልክ በማስተሰረያና ማጣጣሚያ ትግበራ ላይ እንደሚታዩት ችግሮች ሁሉ ከአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ ጋር በተያያዘ ከኪሳራና ጉዳት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ለመፍታት ችግር እየገጠመ ይገኛል።

በኮፕ 26 የተለየ የፋይናንስ ፋሲሊቲ በማቋቋም የኪሳራና ጉዳት ጉዳዮችን መፍታት የታዳጊ ሀገራት ዋነኛ ፍላጎት ነበር። የዋርሶ አለም አቀፍ የኪሳራና ጉዳት ማስፈጸሚያ መንገድ በ COP19 የተመሰረተ ሲሆን፣ የሳንቲያጎ የኪሳራና ጉዳት ማእቀፍ ደግሞ በ COP25 ተመስርቷል።

የCOP26 ውጤቶች:

- እየተስተዋለ የሚገኘው የአየር ንብረት ለውጥ ኪሳራና ጉዳት እንደሚያስከትል እሙን ነው። ካሉት ምንጮችም በተጨማሪ ይህን ኪሳራና ጉዳት ለመመከት ገንዘብ እንደሚያስፈልግ በግልጽ ተቀምጧል።
- የሳንቲያጎ ማእቀፍ ተግባራት እና የገንዘብ ድጋፍ ዝግጅት ላይ ስምምነት ተደርሷል። የሳንቲያጎ ማእቀፍ አባል ሃገራት ኪሳራና ጉዳትን ለማስቀረት እና ለመቀነስ እንዲችሉ የቴክኒክ ድጋፍን ያመቻቻል።
- የግላስጎ ውይይት አባላት፣ የሲቪክ ማህበር እና ባለሙያዎች ቡድን ተቋቁሟል።
- ታዳጊ ሃገራት ለኪሳራና ጉዳት የተለየ የፋይናንስ ፋሲሊቲ እንዲቋቋም የጠየቁ ሲሆን ስምምነት ላይ ግን አልተደረሰም።

2.8 የአቅም ግንባታ

የCOP26 ስብሰባ ያተኮረው የፓሪስ የአቅም ግንባታ ስምምነትን እ.አ.አ ከ2021–2024ን ሞተግበር ላይ ነበር።

የCOP26 ውጤቶች:

- አባል ሀገራት በአቅም ግንባታ ዙሪያ የመናበብና ቅንጅታዊ አሰራር አስፈላጊነት ላይ ተስማምተዋል።
- አባል ሀገራት ታዳጊ ሀገራት ያለባቸውን ክፍተት እንዲለዩና ይህንንም እንዲቀርፉ ድጋፍ መሰጠት እንዳለበት ተስማምተዋል።
- የአባል ሀገራት የአቅም ግንባታ ተግባራትን ወደፊት ለማራመድ ያሳዩት ጠንካራ አቋም በመልካም ተወስዷል።
- ይህንንም በታዳጊ ሀገራት የሚስተዋለውን የአቅም ክፍተት ለመፍታት እና የፓሪስ ስምምነትን ለማስፈጸም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የድህረ ምረቃ ፕሮግራም ለመጀመር አስቧል።

ማጠቀለያ፡ ኢትዮጵያ በተለያዩ ርዕሶች ዙሪያ ከኮፕ 26 የምትጠብቃቸው ጉዳዮች ላይ መሻሻሎች ታይቷል። ምንም እንኳን በርካታ ውይይቶች እና ስምምነቶች ገና መደረግ ቢኖርባቸውም፤ የኮፕ 26 ውጤቶች እንደሚያሳዩት ከባለድርሻ አካላት አበረታች ቁርጠኝነትና ከአብዛኞቹም በተጨባጭ ተግበራትን ለማከናወን ፍላጎቶች ታይተዋል።

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፪፣ ቁጥር ፭

ሁነቶች

የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በዓለማቀፍ ደረጃ መከሰቱንና በፍጥነት መስፋፋቱን ተከትሎ በርካታ የአየር ንብረት ለውጥና ዘላቂ የአካባቢ ልማትና ጥበቃን የተመለከቱ ሁነቶች በመረጃ ቴክኖሎጂ በመታገዝ እየተካሄዱ ናቸው። የሚከተሉት በበይነ መረብ አማካይነት የሚከናወኑ ሁነቶች ለማናቸውም ታዳሚዎች ተደራሽ ናቸው። እያንዳንዱን ሁነቶች አስመልክቶ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ ‹ምንጭ› የሚለውን ማስፈንጠሪያ ይክፈቱት።

- ቴራ ፈንድ ለ ኤ.ኤፍ.አር.100፡ የአፍሪካን መልክዓ ምድሮች መልሰው የሚያለሙ ፈጣሪዎችን በገንዘብ መደገፍ፣ ደብልዩ.አር.አይ.፣ ጥር 2022 | ምንጭ
- የውጭ ፖሊሲ ምክክር: የዜሮ ካርቦን ዳይኦክሳይድ ልቀት ወደሚያመራው መንገድ፤ ሃይንሪች ቦል ፋውንዴሽን፣ ጥር 2022 | ምንጭ
- አምስተኛው የመንግስታት ግምገማ ስብሰባ በአለምአቀፍ የድርጊት መርሃ ግብር ትግበራ፣ ዩ.ኤን.ኢ.ፕ፣ የካቲት 2022 | ምንጭ
- በተገቢ ምርመራ የተደገፉ የተዘዋዋሪ የንግድ ሥራ ሞዴሎች - ምስክርነት ከአፍሪካ ጥቃቅን እና መካከለኛ የጨርቃጨርቅ ድርጅቶች፣ ዩ.ኤን.ኢ.ፕ፣ የካቲት 2022 | ምንጭ
- የአፍሪካ ሴቶች መብቶች እና በዘላቂ ልማት ውስጥ ያላቸው ሚና፣ ዓለም አቀፍ የምርምር ማበልፀጊያ እና የእውቀት ልውውጥ ምሁራን፣ መጋቢት 2022 | ምንጭ
- እ.አ.አ. የ2022 የአየር ንብረት ለውጥ ሳምንት፤ የዓለም የአየር ንብረት ለውጥ እና የዘላቂነት ምክክር፣ ክላይሜት ሊንክስ፣ እ.አ.አ. ነሐሴ 2022 | ምንጭ

ከ26ኛው ዓለም ዓቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ ጎንዮሽ የነበረው የኢትዮጵያ ተሳትፎ ዳሰሳ - "የፓሪስን ግቦች ከማሳካት አኳያ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና የመሬት አጠቃቀም ሚና"

❑ በአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን

ኢትዮጵያ በ26ኛው ዓለማቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ ወቅት በዋናው ድርድር ላይ ካላት የነቃ ተሳትፎ በተጨማሪ በተለያዩ የጎንዮሽ ዝግጅቶች፣ የሁለትዮሽ ውይይቶች እና የጉባኤው ፕሬዝዳንት ዝግጅቶች ላይ በንቃት ተሳትፋለች። ይህ መጣጥፍም በ26ኛው ጉባኤ ወቅት ጉባኤውን በጠራው አካል የተመራውንና ኢትዮጵያም ተሳትፎ ያደረገችበትን የተፈጥሮ ሀብትና የመሬት አጠቃቀምን የሚመለከተውን ዝግጅት ይዳስሳል።

እ.አ.አ ህዳር 6፣ 2021 የተከናወነው ይህ ሁነት መንግስታት፣ ሳይንቲስቶች እና ሌሎች ተዋናዮች እንዴት በተፈጥሮ ላይ በመስራት የአየር ንብረት ለውጥን ተፅዕኖ ለመቀነስ እና የሙቀት አማቂ ጋዞችን የልቀት መጠን በ1.5 ዲግሪ ለመግታት የተቀመጠውን ግብ ብዝሀ ህይወት ሳይቃወስና በሚሊዮኖች የሚቆጠሩና ኑሯቸው በመሬት ላይ የተመሠረተ ሰዎች ጉዳት ሳይደርስባቸው እየሰሩ እንደሆነ ለመዳሰስ ታስቦ የተዘጋጀ መድረክ ነው። በዚህ ሁነት ላይ በተፈጥሮ እና ተፈጥሮን መሰረት ባደረገ የመፍትሄ ሃሳቦች ላይ ያላቸውን መልካም ተሞክሮ እንዲያካፍሉ ከተጋበዙ ጥቂት ሀገራት መካከል ኢትዮጵያ አንዷ ነበረች። በዚሁ መሠረት የኢትዮጵያ የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ኮሚሽነር ክቡር ፕ/ር ፍቃዱ በየነ በመድረኩ ላይ ተሳትፈው ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል እና የፓሪሱን ስምምነት ከግብ ለማድረስ የተፈጥሮ ሀብቶችን በመጠበቅና መልሶ ከማልማት ረገድ ያደረገቻቸውን ጥረቶችና የተመዘገቡ ውጤቶችን ለታዳሚዎች አካፍለዋል።

በሁነቱ ላይ ከተለያዩ ሀገራት አገር በቀል እና ከአካባቢው ማህበረሰብ የትስስር መረቦች እና ከተቋማት የተውጣጡ ጠንካራ የልምድ ልውውጦች፣ የትግበራ መሳሪያዎች አጠቃቀም፣ የለውጥ ፍላጎቶችን እና በመሬት ላይ እየተተገበሩ የሚገኙ ጅምር ስራዎች ልምዶችና የተመዘገቡ ውጤቶች ተካተው ቀርበዋል። በመድረክ ልምዳቸውን ቀርበው ካካፈሉ ሀገራት ውስጥ ሲሼልስ፣ ቤሊዝ፣ ካናዳ፣ ባንግላዲሽ እና ቦሊቪያ ይገኙበታል። በተጨማሪም የኢንዶኔዥያ እና


ወደ ገፅ ፯

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፪፣ ቁጥር ፮


ልዩ ልዩ ሀትመቶች

የታዳሽ ኢኮኖሚዎች ፍኖተ ካርታ፤ በጥናት ላይ የተመሠረቱ "ኤን.ዲ.ሲ.ዎች"




የጀርመን መንግስት የሁለትዮሽ የጋራ ትብብር ድርጅት (GIZ) በፓሪሱ ስምምነት መሰረት የታዳሽ ኢኮኖሚ እርምጃዎችን "ከኤንዲሲዎች" ጋር ለማጣጣም የሚያስችል ፍኖተ ካርታ አውጥቷል። ይህም የታዳሽ ኢኮኖሚ አቀራረቦችንና ትግበራን ለመደገፍ የፖሊሲ መሳሪያዎች፣ የሂሳብ አያያዝ ዘዴዎች እና የታዳሽ ኢኮኖሚን ለማቀድ የዘርፍ እና ንዑስ-ሀገራዊ ትብብር ሂደቶችን የሚያሳይ ነው። ምንጭ

ሰባቱ ተራማጅ ለውጦች ለፍትሃዊ እና ዘላቂ ከተሞች



በ160 ደራሲያን እና ገምጋሚዎች የተካሄደውን የስድስት አመታት ጥናት መሰረት በማድረግ በከተሞች ውስጥ ተራማጅ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል ፍኖተ ካርታ ከዓለም ሃብት ኢንስቲትዩት የተገኘው አፅርኦተ ዘገባ አሳይቷል። ። ምንጭ

የንግድ ሚና በማደግ ላይ ላሉ አገሮች ከቀውስ እንደ ማገገሚያ አማራጭ



የዓለም ባንክ ቡድን እና የዓለም ንግድ ድርጅት (WTO) አዲስ የፖሊሲ፣ ዓለም አቀፍ ንግድ እና ዓለም አቀፍ የእሴት ሰንሰለቶች መፋጠን ድህነትን ለመቀነስ፣ ዘላቂ ልማት ለማምጣት እና በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት የደረሠውን የኢኮኖሚ ቀውስ ለማገገም ያለው ሚና ላይ ያተኩራል። ምንጭ

ከገፅ ፭ የቀጠለ

የዲሞክራቲክ ኮንጎ ሪፐብሊክ ሀገር በቀል የማህበረሰብ ትስስር መረቦች ተወካዮች ተገኝተው ልምዶቻቸውን፣ ያጋጠሟቸውን ተግዳሮቶች እና ምክሮቻቸውን አካፍለዋል።

በዝግጅቱ ላይ ኢትዮጵያን በመወከል የተሳተፉት ክቡር ፕሮፌሰር ፈቃዱ በየነ በኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥንና የብዝሀ ህይወትን ቀውስ እንዲሁም የአጠቃላይ የእድገት ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ ተፈጥሮ ያለውን ዋጋ በሚገባ ተገንዝቦ እየሰራች መሆኑን ለተሳታፊዎች አብራርተዋል። ክቡር ፕሮፌሰሩ በማብራሪያቸው እንደገለፁትም በፖሊሲ ደረጃ በኢትዮጵያ እ.አ.አ. ከ2011 ጀምሮ በመተግበር ላይ የሚገኘውና እ.አ.አ. እስከ 2030 የሚተገበረው ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ልማት ስልት (CRGE) የተራቆቱ መሬቶች መልሰው እንዲያገግሙ የሚያስችለውና የደን ሀብትን ለመጠበቅ የሚያስችሉ ስራዎችን ለመስራት የሚቻልባቸውን ሁኔታዎች በግልፅ እንደ ዓላማ ማስቀመጡን ገልፀዋል።

ክቡር ፕሮፌሰር ፈቃዱ አያይዘውም እንደገለፁት ኢትዮጵያ ብሄራዊ የREDD+ ስትራቴጂ፣ ሀገር አቀፍ የደን ልማት መርሃ ግብር፣ ብሄራዊ በፍቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ መቀነሻ እቅድ፣ ሀገር አቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ የማጣጣሚያ እቅድ፤ በቅርቡ ወደተግባር የገባው ሀገራዊ መሪ የልማት ዕቅድና የተከለሠው በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ መቀነሻ ዕቅድ የሚባሉት በሙሉ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃንና ዘላቂ የመሬት ሀብት አጠቃቀምን በሚገባ አካተው የተዘጋጁ ናቸው። ከነዚህም በተጨማሪ ኢትዮጵያ የተራቆተና ገላጣ መሬትን በደን መልሶ ለማልማት "የአፍሪካን መሬት በደን መልሶ መሸፈን ለሚል ኢኒሼቲቭ (AFR100)፣ በቦን ቻሌንጅ እና 15 ሚሊዮን ሄክታር የተጎዳ መሬትን መልሶ በደን ለመሸፈን ያለመውን የኒውዮርክ የደን ልማት ስምምነት ለማሳካት ኢትዮጵያ የበኩሏን አስተዋጽኦ ለማድረግ ያላት ቁርጠኝነት በሀገሪቱ ህጎች፣ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች በጉልህ ተለይቶ ተቀምጧል።

ኢትዮጵያም በዚህ መድረክ ያላትን ተግባራዊ ተሞክሮም ያካፈለች ሲሆን እነዚህም የአየር ንብረት ለውጥን ለማጣጣም እና ለማስተሠረይ የሚረዱ መጠነ ሰፊ የችግኝ ተከላ ዘመቻዎች፣ የተፋሰስ መልሶ ልማት እና ጥበቃ፣ የመሬት ክለላ፣

ወደ ገፅ ፮

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፪፣ ቁጥር ፮

ከገፅ ፭ የቀጠለ

የሀገር በቀል እፅዋትን ተፈጥሯዊ ጥበቃን የሚያጎለብቱ የአፈር ጥበቃ ዘዴዎች እና ለገበያ የሚውሉ የዛፍ እርሻዎችን በእርሻ ማሳዎች እና በመኖሪያ ቤቶች ዙሪያ የማስፋፋት ስራን ያካትታሉ። ከነዚህ በርካታ ስኬታማ ልምዶች. በተጨማሪም ኢትዮጵያ እ.አ.አ በ2022 ሀያ ቢሊየን ችግኞችን የመትከል ዓላማ ያለው ሀገራዊ ግብ በማስቀመጥ እ.አ.አ ከ2019 ጀምሮ "አረንጓዴ አሻራ" የሚል መሪ ሀሳብ የተሰጠው ብሄራዊ የችግኝ ተከላ ስትራተጂካዊ እርምጃና ስኬቶቹ ለአለም አቀፍ ታዳሚዎች በመድረኩ ቀርቧል።

ፕሮፌሰር ፍቃዱ በመድረኩ የማጠቃለያ ንግግራቸው ኢትዮጵያ ተፈጥሮን ለመጠበቅ እና ወደነበረበት ለመመለስ እንዲሁም የብዝሀ ህይወትን ለመጠበቅ ያላትን የማይናወጥ ቁርጠኝነት ገልፀው ከተፈጥሮ ጋር ተስማምቶ ለመኖር በመድረኩ ላይ የተሳተፉ ባለድርሻ አካላትም ይህንን አላማ እንዲጋሩ ጠይቀዋል።

ይህ ሁነት ተፈጥሮን መሰረት ያደረጉ መፍትሄዎችን አስፈላጊነት እና ከአካባቢው ማህበረሰቦች ጋር የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያና ማስተሠርያ ስራዎችን በቅርበት ተቀራርቦ መስራት እንደሚያስፈልግ አሳይቷል። ይሁንና ተፈጥሮን መሠረት ያደረጉ መፍትሄዎች ከሚያጋጥሟቸው አበይት ተግዳሮቶች አንዱ መፍትሄዎቹ በዘርፉ ከሚመደበው የዓለም ፋይናንስ ውስጥ 3% ያህሉን ብቻ ስለሚደርሳቸው ነው።

ይህ ተግዳሮት እንደተጠበቀ ሆኖ በመድረኩ ላይ አንዳንድ ተስፋ ሰጪ አዝማሚያዎችም ተንፀባርቀዋል። የዘርፉ ዘገባዎች እንደሚያመላክቱት እ.አ.አ እስከ ጥቅምት 2021 ለተመድ የአየር ንብረት ለውጥ ማዕቀፋዊ ስምምነት ሴክሬተርያት ከቀረቡት በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ መቀነሻ እቅዶች ውስጥ 92 በመቶ ያህሉ ተፈጥሮን መሰረት ያደረጉ መፍትሄዎችን ያካተቱ ሲሆን ይህም ቀደም ብለው ከቀረቡ ዕቅዶች የ10 በመቶ እድገት አሳይቷል። ከዚህም በተጨማሪ ሪፖርቱ እንደሚያመላክተው 88% የአካባቢ ነባር ነዋሪ ማህበረሰብ አካላትን ታሳቢ አድርገው የታቀዱ ናቸው።

ከመሬት አጠቃቀም ጋር በተገናኘ 25% የሚሆነው የአለም ሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀቶች በተፈጥሮ እና ከመሬት ጋር የተያያዙ በመሆኑ በተፈጥሮና መሬት ላይ አትኩረው የሚተገበሩ የአየር ንብረት እርምጃዎች በየአመቱ ከሚለቀቀው የሙቀት አማቂ ጋዞች መጠን ውስጥ 10 ጊጋ ቶን ያህል የካርቦን ልቀትን ለመቀነስ የሚያስችል አቅም እንዳላቸው ይገመታል። ይህ እውነታም የመሬት አጠቃቀም ስርዐታችን ለአለም አቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ መጠበቅ ያለውን ከፍተኛ አዎንታዊ ሚና በግልፅ ያሳያል።

ከዚህም ባሻገር መሬት እና ውቅያኖሶች በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን የኑሮ ዘይቤ የተመሠረተባቸው እና ለአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣምን አስፈላጊ ጉዳዮች ናቸው። በቅርቡ የተካሄደው የመንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ ፓናል (IPCC) ሪፖርት እንደሚያሳየው የአየር ንብረት ለውጥና የብዝሃ ህይወት ጥበቃ ጎን ለጎን መሰራት አለባቸው። በተጨማሪም ተፈጥሮን መሰረት ያደረጉ መፍትሄዎች በውጤታማነት ሊሰሩ የሚችሉት ከአካባቢው ማህበረሰቦች ጋር በቅንጅት ሲሰሩ ብቻ እንደሆነ አፅንኦት ሰጥቷል።

በመድረኩ ላይ ተገኝተው መልዕክት ያስተላለፉት የ26ኛ የዓለም የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ ሊቀመንበር ተወካይ እንዳሉት የግሉ ዘርፍን ጨምሮ ከአለም ዙሪያ ተፈጥሮን መሰረት ያደረጉ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ መቀነሻና መቋቋሚያ መፍትሄዎችን ለመደገፍ አስደናቂና ቁርጠኝነት ታይቷል። በመሆኑም ይህ በ26ኛው የአባል ሀገራቱ የጉባኤው ወቅት የተገኘው ድጋፍ ያለውን የሀብት ክፍተት ያጠባል ተብሎ ይጠበቃል።

በመሆኑም እነዚህ በጉባኤው ላይ የተገቡ ቃል ኪዳኖች እውን ከሆኑ ሀገራዊ በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረቱ አየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ እቅዶቻቸውን ለመተግበር የገንዘብ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው አገሮች በእውነት ታላቅ ዜና ነው። ኢትዮጵያም እቅዶቿን ለመፈፀም ከሚያስፈልጋት ገንዘብ መሃከል 80% ያህሉን ከለጋሾች ማግኘት ስለሚያስፈልጋት ከተጠቃሚዎቹ መሃከል ትሆናለች።

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

የኢፌዲሪ የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን

ሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት

ፖ.ሳ.ቁ : 12760, አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ስልክ ቁጥር: +251 11-170-4038/4150

ኢሜል: efcccethiopia@gmail.com

ድረ ገፅ: https://www.efccc.gov.et

ሀላፊነት ስለመውሰድ

በዚህ ህትመት ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች የግድ የኢትዮጵያን መንግስት ኦፊሴላዊ አመለካከቶችና ፖሊሲዎች የሚወክሉ አይሆኑም። በተጨማሪም ሌሎች ሀገራትንና ተቋማትን የሚመለከቱ አንዳንድ ይዘቶች ቢኖሩ እነዚህ ሀገራቱን የተመለከቱ ጉዳዮች የሀገራቱን የህጋዊ መብት የሀገር ድንበር፣ ወይም ከተማና የስልጣን ሁኔታዎች የኢትዮጵያ መንግስትንም ሆነ ህትመቱን በገንዘብና በቴክኒክ የደገፉ ተቋማት ፖሊሲዎች ወይም አቋሞችን የሚወክሉ አይደሉም።

ስራውን የደገፉ አካላት

NDC PARTNERSHIP | IN CONTRIBUTION TO THE NDC PARTNERSHIP

MINISTRY OF FOREIGN AFFAIRS OF DENMARK | Federal Ministry for Economic Cooperation and Development | Supported by: Federal Ministry for the Environment, Nature Conservation and Nuclear Safety | Ministry of Foreign Affairs of the Netherlands | Norwegian Ministry of Climate and Environment | Norwegian Ministry of Foreign Affairs | Government Offices of Sweden Ministry for Foreign Affairs | UK Government

based on a decision of the German Bundestag

CDKN Climate & Development Knowledge Network

SOUTH SOUTH NORTH TOWARDS CLIMATE RESILIENCE

Funded by

Ministry of Foreign Affairs of the Netherlands

IDRC · CRDI International Development Research Centre Centre de recherches pour le développement international

Canada

This work was carried out with the aid of a grant from the Ministry of Foreign Affairs of the Netherlands and the International Development Research Centre (IDRC), Canada, as part of the Climate and Development Knowledge Network (CDKN) Programme. The views expressed herein do not necessarily represent those of the Ministry of Foreign Affairs of the Netherlands, or of the International Development Research Centre (IDRC) or its Board of Governors, or of the entities managing CDKN.